የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ትብብር - ዴሞክራሲያዊ ምትሕብባር ትግራ

TIGRIAN ALLIANCE FOR NATIONAL DEMOCRACY

( TAND )

# ሁሉም ፓርቲ በሃገር ጉዳይ ላይ በጋራ ይቁም

ለህዝብ የቆመ መንግስት ኖረም ኣልኖረም ሁሉም ዜጋ በጋራ የሚቆሙለት ሃገራዊ መርሆች ና አቋሞች ምንጊዜም ይኖራሉ። የሃገር ልእልና የሚጠበቀውና የሃገር ህልውና የሚከበረው ሁሉም ዜጋ ሃገር ለሚያሰኙ የጋራ እምነቶቹ ተባብሮና ተደጋግፎ ሲቆም ብቻ ነው ። ጥልቀትና ስፋት ያላቸው ሃገራዊ እምነቶች ጠንቀቆ ማወቅ፤ መንከባከብና ኣሉታዊ የሆኑ ስብከቶች በማስተጋባት እንዳይሸረሸሩ መጠንቀቅ የሁሉም ዜጋ ሃላፊነት ነው። አለዚያ ሃገር አለኝ ብሎ በማንነቱ መኩራራቱ ብቻ ከንቱ ውዳሴ ከመሆን አያልፍም።

በአሁኑ ወቅት የኣፈናና የንቅዘት አባወራዎቹ ፣ አወናባጁ መለስ ዜናዊና መሰሪው ስብሓት ነጋ ለዘረፋው ይመቻቸው ዘንድ ኢህኣዴግን ብቻቸውን ተቆጣጥረው ኢትዮጵያን በሁሉም አቅጣጫ እያቆሰልዋት ይገኛሉ ። ህዝቡም መብቱ ተነጥቆ ፣ ኣይቶት በማያውቀው የመከራ ማጥ፥ ረሃብ ፣ በሽታ ፣ ስራ ኣጥነት ፣ አፈና ውስጥ ተዘፍቆ እንዲኖር ተገደዋል ። ሃገራዊ ማንነቱ ተከብሮና ተባብሮ ለዘላቂ እድገት በጋራ እንዳይሰለፍ አምባገንኖቹ ሀጋዊ በሆነ መልኩ ጭምር ከፋፋይ ፖሊሲ ዘርግተው ህዝቡን ኣበጣብጠውታል ። ለሃገር ልእልና ለህዝብ መብት መከበር በሚከራከሩ ሃገር ወዳድ ወገኖችን ላይ ተልካሻ ምክንያት እየጠነጠኑ የእስር፣ የግድያ፣ የጥፋት ሰለባ አድርገዋቸዋል። አምባገነኖቹ በሀገራችን ላይ የፈጠሩት ችግር ማለቅያም የሌለው ሆኖዋል።

ከዚህ አሳፋሪና ዘግናኝ የሃገራችን ሁኔታ ለመላቀቅ አያሌ ተቃዋሚ የፖለቲካ ሃይሎች በተናጠልም *በህብረትም* ሲታገሉ ቆይተዋል ። ጥግ ይዞ መተቸት ሳይሆን አምባገነኖቹን ለማጋለጥና ለማስወገድ ብዙ መስዋእትነትም ከፍለዋል። በርግጥ ሀገራችንን ከዚህ ሁሉ መከራ ሊያላቅቁና እርባና ያለው ለውጥ ሊያመጡ አልቻሉም። እስካሁን የተያዘው የትግል ዘይቤም እንዲሁ ከቀጠለ በአምባገነኖቹ ስትራተጂያዊ ወጥመድ ተሰክቶ ትግልን ማራዘም ወይም መተራመስ እንጂ ሃገር የምትጠብቀው፣ ህዝብ የሚመኘው ብሩህ ተስፋ እውን ሊሆን እንደማይችል የአስር አመቱ የትግል ውጣውረድ በቂ ማስረጃ ነው።

ይህ አሳዛኝ እውነታ ብዙ ጥያቄዎችን ያስነሳል። ሁሉም አገር ወዳድ አንዴ ቆም በማለትየ ት ላይ ነው ችግሩ፣ ምንስ ማድረግ ይገባኛል ብሎ ጉዞውን እንዲመረምር ያስገድዳል ። በቅድሚያ ተመሳሳይ አቋም ያላቸው ድርጅቶች ለምን ህብረት ሊመሰርቱ ባወጁት ተመሳሳያ አቋም ሊዋሃዱ አልቻሉም፣ ቀጥሎም ሁሉም ድርጅቶች ሃገር አቀፍ ጉዳይ ላይ ባንድ ማእከ ል ተቀናጅተው አንድ ድምጽ ሆነው ለምን አይሰለፉም፣ ሃገራዊ ህብረት እንዳይፈጠር እን

ቅፋት የሆነው ምን ወይም ማን ነው፣ ህብረት መስርቶ ታግሎ ሃገር በታኞችን ማስወገድ
ካልተቻለ ሃገርን በጋራ መገንባቱ ይቅርና ሃገር አለኝ ማለቱስ የት ላይ ነው፣ እነዚህና
መሰል ጥያቄዎች ሀገሩን የሚያፈቅር ሁሉ ነጋ ጠባ የሚያነሳቸው ጥያቄዎች ቢሆኑም አሁን
የምንገኝበት የተዝረከረከ ሩጫና ትርምስ ሁነኛ መልስ እንዳይሰጥበት አግደዋል። ለምን።
በችግሩ መግባባት አጥተን ይሆን መፍትሄው የራቀብን።

ሃገር እየተናደ ህዝብ እያለቀ፥ ባለንበት ተቆላልፈን እንድንቀመጥ ችግር የፈጠረብንን ምክ
ንያት አበክሮ ማወቅ የመፍትሄው ቅድመ ሁኔታ ነውና ከብዙ በጥቂቱ የተገነዘብናቸውን ጠ
ንቆች በጥቂቱም ቢሆን መጥቀሱ ተገቢም ጠቃሚም ነው እንላለን። ሌላውም እንደዚሁ ዳር
 ዳር ከማለት የሚታየው ችግርና መፍትሄ ቢሰነዝር ቁልፉን የሚያስጨብጥ መልካም የትግ
ል ምዕራፍ ይመስለናል።

በህዝብና በመንግስት መካከል እንደዚሁም በህዝብና በድርጅት መካከል ያለውን እጅግ ሰፊ
ልዩነት ጠንቅቆ ባለማወቅ የሚካሄደው ልፈፋ ለህብረት ትግላችን ጠንቅ እንደሆነ ሁሉ በሃ
ገር ጉዳይና በድርጅት ጉዳይ መካከል ያለው ልዩነትም በአግባቡ ባለመቀመጡ ለህብረት ት
ግሉ አሰናካይ ሁኔታ ፈጥረዋል። ሃገር የሁሉም ዜጋ የዘለአለም ቤትና የማንነቱ አርማ መ
ሆኑን ዘንግተው፥ ከኛ ወዲያ ኢትዮጵያዊ ለአሳር ብለው ድርጅታቸው ብቻ የበላይ
ኢትዮጵያዊ አድርገው የሚቆጥሩ አሉ። የነዚህ ድርጅቶች ሃገራዊ ፍቺ ዋናው ችግሩ ሌላውን
ኢትዮጵያዊ የበታች አድርጎ ስለሚከፋፍል፥ አቀንቃኞቹ አምባገነንነት ማርገዛቸው ከወዲሁ
ይታይና የህብረቱ የማይለቅ ቁስል ይሆናሉ። አንዳንዱ *ፖለቲከኛም* ድርጅት ውስጥ የተወለ
ደ፥ የሚኖርና የሚቀበር ይመስል በቅድምያ ለድርጅቱ በስሜት ሲዋደቅ አውቆም ይሁን ሳ
ያውቅ ታላቁን የሃገር ጉዳይ ደብዛ ያሳጣዋል። የታሪክ፥ የስምና ገናለገና የስልጣን ሽምያም
የማስቀደም ነጸብራቅ አልጠፋም።

ሃገር የሚለው ጥልቅና ሰፊ አምር እንዲሁም ሃገራዊ ጉዳይ ማለት በዚያች ሃገር ውስጥ
ለተፈጠረው ዜጋ ሁሉ እኩል የሚመለከተው የጋራ ጉዳይ መሆኑን ጠንቅቆ ማወቅና ማሳወ
ቅ፤ ለሃገር እርባና ሲባል ድርጅታዊ መርሆችና አቋሞችን አቻችሎ መራመዱ የእውነት
ሃገር ወዳድናት መሆኑ ይታወቅ እንላለን። ማንም ኢትዮጵያዊ በግለሰብም ይሁን በስብስብ
መሰረታዊ መብቱን ለማስከበር ሃገራዊ መሰረቱን ሳይለቅ መታገሉ አገባብ ያለው ጥያቄ እ
ንጂ እንዲሁ የብተና ስራ አለመሆኑ ግልጽ እንዲሆንም ይገባል። እነዚህ ግንዛቤዎችን አጣጥ
ሞ በተግባር ማሳየት ካልተቻል ከትርምሱ መላቀቅ አይቻልም።

ከዚህ ከባድ ችግር ጋር በተያያዘ መልኩ ከቅርብ ጊዜ በፊት ድርጅታችን ት ዴ ት የህብ
ረቱ ሂደትና የውህደት ጥያቄ እንዲሁም ርብርቡ ወደ መሰረታዊ መፍትሔ ማቅናት አለበት
በሚሉ ርእሶች ላይ ለህብረታችን እንቅፋት የሚፈጥሩ ደንቃራ አመለካከቶችን ዘርዝሮ
ከማስፈሩ ባሻገር ከስህተቶቻችን ተምረን ህብረታችንን እንድናጠናክርና ወደ ሀገራዊ ውህደትየ
ምንሸጋገርበት አንቅጾ (initiative) መውሰዱንም ይፋ አድርገዋል ። የውህደቱ ጥሪያ
ችን ማለትም በዴሞክራሲያዊ አቋሞች ላይ የተመሰረተ ሃገር አቀፍ ድርጅት በጋራ ፈጥረ
ን የመታገሉ አስፈላጊነት ጠርዝ ላይ ያላችውን ሃገራችንን ፈጥኖ የማዳን አንገብጋቢ ጥያቄ
በአጽናኦት አስምሮበታል። ት ዴ ት ለዚህ ወሳኝ ጥሪ አወንታዊ መልስ ወይም አማራጭ
ጥሪ እንዲቀርብለት አሁንም እየጠበቀ ነው።

ሃገር በህዝቡ ተሳትፎና በዘለቄታዊ ስርአት የሚተዳደርበት፣ ሰባዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች
የሚከበሩበት፣ የዜግነት መብትና ግዴታ የሚጠበቅበት፣ የህግ የበላይነት የሚረጋገጥበት፣

ሕገ መንግስትና ተቋማቱን ስራ ላይ ማዋል ያንድ የተወሰነ ቡድን ቅባት ሳይሆን የሁሉም ዜጋ የጋራ ሃገራዊ ጉዳይ መሆኑ ይታወቅ። ሃገራዊ ጉዳይ በመሆኑም ለተገባራዊነቱ ሁሉ ዜጋና ድርጅቶቹ እኩል መረባረብ ይኖርባቸዋል ። አንድ ወይም ሁለት ድርጅት ብቻ የሚ መጻደቅበት የግል ፕሮጀክት አይደለምና። ይህ ሃገር አቀፍ አላማ ከድርጅት ይሁን ከማህበ ር አላማ እጅግ የላቀና ዘላቂ ጉዳይ መሆኑ ተቀብሎ ተግባር ላይ ለማዋል የሚያስችል፣ የጋ ራ አቋምና እቅድ ለመንደፍ ሁሉም ፓርቲ አቀፍ ጉባኤ እንደሚያስፈልግ አያጠያይቅም ።

በቅርቡ እንዲሰየም የታቀደው ሁሉም ፓርቲ አቀፍ ጉባኤ እስካሁን የመጣንበትን ሸካራ የህብረት ጉዞ በማያዳግም ሁኔታ ገምግሞ ፣ ያለፉት ስህተቶች እንዳይደገሙ ገደብ አበጅቶ ለሀገራችን የሚበጅ ዘላቂ መፍትሔ ቀይሶ ተግባር ላይ እንደሚያውል ጽኑ እምነት አለን። ይህ አንቅጾ ወሳኝ ሃገራዊ ጉዳይ በመሆኑ ማንም ኢትዮጵያዊ በርቀት ሳይሆን በቅር በት፥ በደፈናው ሳይሆን በዝርዝር ሂደቱን እየተከታተለ፥ ድጋፍም ይሁን ሂስ እያከለ፥ ለስ ኬታማነቱ ተግባራዊ ተሳትፎ እንዲያደርግ ከወዲሁ እናሳስባለን።

ት ዴ ት የዚሁ የሁሉም ፓርቲዎች ጉባኤ መሳካት ሀገራችንን ከአምባገነኖቹ ጥላ አላቅቆ እድገቱዋን ፈር ለማስያዝ ለሚደረገው ከባድ ትግል፥ አንድ ትልቅ እርምጃ አድርጎ ስለሚያየው እንደወትሮው ያላሰለሰ ተሳትፎ እንደሚያደርግ ያረጋግጣል ።

ት ዴ ት<br>
ሚያዝያ 2002